**Amharic**
**መጋቢት 2023**

# የአውስትራሊያን የመድሃኒት አሰራር ስርአት መረዳት

- **አስተርጓሚዎች**
- **Medicare**
- **የዋጋ ቅናሽ ካርድ**
- **ወደ ዶክተር ስለመሄድ**
- **መድሃኒትዎን ስለማግኘት**
- **ልዩ ባለሙያዎች**



የአውስትራሊያ ህክምና አሰራር ስርዓት ውስብስብ ነው። እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ ከታመሙ፣ እርዳታ ለማግኘት ወዴት መሄድ እና ምን ያህል እንደሚያስከፍል ለማወቅ ያስቸግራል። ይህ መረጃ በጥቂቱም ቢሆን ስለ አውስትራሊያ የህክምና አሰራር ስርዓት እንዲያውቁ ይረዳዎታል።

**በቪክቶሪያ ለሚገኙ ጥገኝነት ጠያቂዎች ማስታወሻ**:
በሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ህክምና ማግኘት ይችላሉ። ሌሎች የህክምና አገልግሎቶች በቪዛዎ አይነት ይሆናል። የሚያገኟቸው አገልግሎቶች ከጊዜ በኋላ ሊቀየሩ ይችላሉ፣ ስለዚህ እርዳታ እንዲያገኙ የተመደበልዎትን ደጋፊ ሠርተኛ የትኞቹን ማግኘት እንደሚችሉ ይጠይቁ።

## አስተርጓሚዎች

አስተርጓሚ ከሌሎች ከራስዎ ቋንቋ የተለየ ከሚናገሩ ጋር እንዲነጋገሩ የሚረዳዎት ሰው ነው።

**በአውስትራሊያ፣ አስተርጓሚዎች እውቅናቸውን ለማግኘት የተማሩ ሙያተኞች ናቸው። በአስተርጓሚ በኩል ግንኙነትዎን የሚያደርጉ ከሆነ ጥራት እንዲኖረው ይጠብቃሉ እንዲሁም ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ነው።**

ቋንቋዎን የሚናገር ዶክተር ማግኘት ካልቻሉ፣ **የትርጉም እና አስተርጓሚ አገልግሎትን** (**TIS**) በነፃ በ **131 450** ደውለው አስተርጓሚ ማግኘት ይችላሉ። እንዲሁም ይህ አገልግሎት የህክምና ቀጠሮ ማስያዝ እንዲችሉ ይረዳዎታል።

በአውስትራሊያ በዙ ሰዎች በጤና ስርአት የሚያገለግሉትን ሰዎች ለማነጋገር ይጠቀሙበታል።

አስተርጓሚው ለማንም መረጃዎን **በምንም አይነት** አሳልፎ አይሰጥም። **አገልግሎቱ በነፃ ነው።**

## Medicare ካርድ

Medicare ካርድ ካለዎት፣ ነፃ ወይም በአነስተኛ ዋጋ የሚከተሉትን ዓይነት የህክምና አግልግሎቶች ማግኘት ይችላሉ:

- ነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ የዶክተር ህክምና
- ነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ራጅ እና የደም ምርመራ
- በሕዝብ ሆስፒታሎች ነፃ ህክምና

ወደ ጤና አገልግሎት የሚሄዱ ከሆነ፣ ሁል ጊዜ የ Medicare ካርድዎን ይያዙ።

**Medicare ለሚከተሉት አይከፍልም:**

- የአምቡላንስ ክፍያ
- አብዛኛውን የጥርስ ህክምና
- መነጽር
- በግል ሆስፒታል መቆየት
- እና አንድ አንድ ሌሎች የጤና አገልግሎቶች (ጥያቄ ካለዎት የአጠቃላይ ህክምና ዶክተርዎን ይጠይቁ)

አንድ አንድ ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ እንደ ቪዛቸው ዓይነት Medicare መጠቀም ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ የ የቪክቶሪያ የጥገኞች የጤና መረብን (Victorian Refugee Health Network) ያነጋግሩ።

## የዋጋ ቅናሽ እና የጤና እንክብካቤ ካርድ

**የዋጋ ቅናሽ እና የጤና እንክብካቤ ካርዶች ርካሽ የጤና አግልግሎቶች ያስገኙልዎታል።**

የጤና ካርድ ወይም የጡረታ የቅናሽ ካርድ ካገኙ፣ አንድ አንድ የጤና አገልግሎቶችን ሲጠቀሙ ክፍያው ትንሽ ይሆናል።

ለምሳሌ:


- አንድ አንድ መድሃኒቶችን በርካሽ ዋጋ ያገኛሉ
- በህዝብ የጥርስ ህክምና አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ርካሽ የጥርስ ህክምና እንክብካቤ ማግኘት ይችላሉ

ርካሽ ወይም የነፃ አገልትሎቶችን ለማግኘት፣ ሁልጊዜ የቅናሽ ካርድዎን ያምጡና የጤና አገልግሎቶችን ቅናሽ እንዲያገኙ ያሳዩ።




Medicare card

Medicare ካርድ




Health Care card

የጤና እንክብካቤ ካርድ




Pensioner Concession card

የጡረተኛ የዋጋ ቅናሽ ካርድ

# ወደ ዶክተር ስለመሄድ

**በአውስትራሊያ የቤተሰብ ዶክትሮች አጠቃላይ ሃኪሞች** (GPs) **ይባላሉ። አንድ አንዶቹ ዶክተሮች በጤና ማእከሎች ይሠራሉ፣ አንድ አንዶቹ ደግሞ በራሳቸው ቢሮ ይሠራሉ።**

ካመመዎት ወይም የህመም ስሜት ካለዎት ከዶክተርዎ ጋር ቀጠሮ መያዝ ይችላሉ። እንዲሁም፣ ጤና እንኳን ቢሆኑ ስለጤንነትዎ ማወቅ እና በጤንነትዎ ላይ ምንም ችግር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ዶክተርዎን ማየት ይችላሉ። ዶክተር እራስዎን ከበሽታዎች ለመከላከል፣ ክትባቶች ወይም መከላከያዎች ያስፈልግዎት እንደሆነ በተጨማሪ ሊነግሩዎት ይችላል።

ሴት ወይም ወንድ ዶክተር መምረጥ ይችላሉ።

ዶክተርዎን በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። የሚለውጡ ከሆነ፣ ለአዲሱ ዶክተር የሚወስዷቸውን የመድሃኒት ዝርዝሮች እና የህክምና ሪኮርዶችዎን ይስጡ።

ጤንነት ካልተሰማዎ እና በምሽት፣ በሳምንቱ መጨረሻ፣ እና በሕዝብ በዓላት ዶክተር ከፈለጉ ቀጥለው ከተዘረዘሩት የህክምና አገልግሎቶች አንዱን መጠቀም ይችላሉ።

**በስልክ እርዳታ ለማግኘት:**

- ተረኛ ነርሷን በስ (Nurse on call) ልክ **1300 60 60 24** (በቪክቶሪያ ውስጥ)
- ከሥራ ሰዓት ውጪ የአጠቃላይ ህክምና የእርዳታ መስመር በስልክ **1800 022 222**

**ዶክተሩ እቤትዎ መጥቶ እንዲያይዎ ከፈለጉ።**

- ቤት እየመጣ ለሚያየው ዶክተር (The Home Doctor) በስልክ **13 74 25** ይደውሉ (ቪክቶሪያ ውስጥ)

# ለዶክተሩ ክፍያ ስለማድረግ

የተለያዩ ዶክተሮች የተለያየ መጠን ያለው ገንዘብ ያስከፍላሉ። አንድ አንድ ዶክተሮች በጥቅል (**'bulk bill'**) ያስከፍላሉ። በጥቅል ማስከፈል ማለት Medicare ካርድ ካለዎት አገልግሎቱ በነፃ ነው ማለት ነው።

ቀጠሮ በሚይዙበት ጊዜ ዶክተሩ የጥቅል ክፍያ አገልግሎት ይሰጥ እንደሆነ ይጠይቁ።

ዶክተርዎ የጥቅል ክፍያ የማያደርግ ከሆነ፣ ለህክምናዎ መክፈል ይኖርብዎታል። ከፊሉን ክፍያ ከ Medicare ሊመለስልዎት ይችላል። የጤና አገልግሎቱ የሰጠዎትን ደረሰኝ ያስቀምጡ፣ ምክንያቱም ገንዘብዎን ለማስመለስ ያስፈልግዎታል።

ለMedicare በስልክ **132 011** ዶክተርዎን ካዩ በኋላ ተመላሽ ገንዘብዎን እንዲያገኙ ይደውሉ።



# የዶክተር ቀጠሮ ስለማስያዝ

ለአብዛኛዎቹ የጤና አገልግሎቶች ቀጠሮ መያዝ ይኖርብዎታል። ይህንን መመሪያ በመጠቀም በስልክ ወይም ወደ ጤና አግለግሎቱ በመሄድ ቀጠሮ መያዝ ይችላሉ።

**ቀጠሮ ስለማስያዝ:**

ከዶክተር ጋር ቀጠሮ ሲይዙ፣ የሚከለተሉትን መስጠት ያስፈልግ ይሆናል:

- ስምዎን
- የልደት ቀንዎን
- ሊያዩት የሚፈልጉት ዶክተር
- ዶክተሩን ለማየት የሚፈልጉበትን ቀን እና ሰዓት

**የዶከተር ቀጠሮ በሚይዙበት ጊዜ፣ የሚከተሉትን መጠየቅ ይችላሉ:**

- ዶክተሩ የጥቅል ክፍያ የሚያደርግ ከሆነ
- ካስፈለገዎ አስተርጓሚ እንዲያገኙ

በአውስትራሊያ የዶክተር ቀጠሮ በሚይዙበት ጊዜ፣ በሰአቱ መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው።



## ወደ ልዩ የህክምና ባለሙያ ስለመሄድ

ልዩ የህክምና ባለሙያዎች በተለየ ችሎታ ወይም የጤና መስክ የሰለጠኑ ናቸው፣ ለምሳሌ የልብ ዶክተሮች የልብ በሽታ ባለሙያዎች (ካርዲዮሎጂስት) እና የቆዳ ዶችተሮች (ደርሚቶሎጂስቶች)። በአውስትራሊያ ከልዩ ባለሙያ ዶክተሮች ጋር ቀጠሮ ለመያዝ የዶክተር ምሪት ያስፈልግዎታል።

የምሪቱ ደብዳቤ ለልዩ ባለሙያው ዶክተር ስለ ጤና ችግርዎ ይገልጣል። ዶክተርዎ በሕዝብ ሆሲፒታል የሚያገለግል ልዩ ባለሙያ ዶክተር እንዲያዩ ከፈለገ፣ ያንን ቀጠሮ ይይዙልዎታ። የቀጠሮዎ ቀን በገጠመዎት የጤና ችግር አይነት ይወሰናል።

ዶክተርዎ የግል ልዩ ባለሙያ ዶከተር እንዲያዩ ከፈለገ፣ ለልዩ ባለሙያው ዶክተር እራስዎ ደውለው ቀጠሮ መያዝ ይኖርብዎታል።

## መድሃኒት፣ መድሃኒት ቤቶች እና ኬሚስቶች

በአውስትራሊያ፣ መድሃኒቶችን ወይም ሌሎች የጤና ውጤቶችን የሚገዙባቸው ቦታዎች  መድሃኒት ቤት (pharmacy) ወይም መድሃኒት ቤት ('chemist') ወይም ኬሚስት ይባላሉ። በተጨማሪም፣ መድሃኒት ቤቶችን አስቸካይ ህክምና ለማያስፈልጋቸው፣ እንደ ቁስል፣ በሽታ እና ህመም የነፃ ምክር መጠየቅ ይችላሉ።

ዶክተርዎ መድሃኒት እንዲወስዱ ከፈለገ የማዘዣ ወረቀት (prescription) ወይም ጽሁፍ ('script') ወይም (ጽሁፍ) ይሰጥዎታል። መድሃኒቶቹን ማግኘት ከፈለጉ የማዘዣ ወረቀቱን ወይም ጽሁፉን (prescription) ወይም ('script') በመድሃኒት ቤት ለሚገኙት ሰዎች መስጠት ይኖርብዎታል።

በአውስትራሊያ፣ ሰዎች የሚያስፈልጓቸውን መድሃኒቶች እንዲያገኙ መንግስት ለብዙዎቹ ትእዛዞች ጥቂቱን ወጪ ይከፍላል። የዋጋ ቅናሹን ለማግኘት ወደ መድሃኒቱ ቤት የ Medicare ካርድዎን ይዘው መሄድ አለብዎት።

Centrelink ክ የቅናሽ ካርድ ወይም የጡረታ ካርድ ካለዎት እሱንም ይዘው ይሂዱ። የመድሃኒት ግዢውን የበለጠ ያረክስልዎታል።

ለብዙ መድሃኒቶች ማዘዣ አያሰልግዎትም። እንደ የራስ ምታት ወይም ጉንፋን ለመሳሰሉት ቀላል ህመሞች ያለ ማዘዣ ከመድሃኒት ቤት መድሃኒቶችን መግዛት ይችላሉ። እነሱም ያለ ማዘዣ የሚሸጡ መድሃኒቶች ('over the counter') ይባላሉ።



ይህንን ሰነድ 'የ ኤሲቲ ን የጤና አገልግሎቶች በመጠቀም', 'Using health services in the ACT' በኤሲቲ መንግሥት የተዘጋጀውን እና ለእዚህ ጽሁፍ እንደመረጃ በመሆን የረዳውን፣ እውቅና መስጠት እንፈልጋለን።

centre for culture, ethnicity & health